# ምግታር ለትርምቡሌው ልጅ

እዝራ ደመላሽ - ከፍራንክፈርት


ይቺን በጭቡ የተሠራች ኤርትራ የምትባል "አገር" የባንዳና የትርምቡሌ ልጆች ሲያነቆለጳጵሷት እንደማየት የሰለቸኝ ነገር የለም፡፡ እዚህ ፍራንክፈርት አብሮኝ ነዋሪው ይሄይስ ተአምኖ/ሆሀተ ጥበብ ጌጡ የሆድ ወዳጁ ሀሰን ኡመር አብደላ/የሱፍ ያሲን የታገለለተንና ከፍጻሜ የደረሰለትን የኤርትራ መገንጠል ጉዳይ እባካችሁ አታንሱ ይለናል፡፡ አልፎ ተርፎም የሱፍ ያሲን ለትውልድ አገሩ ለኤርትራ ግንጠላ ስኬት ሽንጡን ገትሮ አቋሙን ያረጋገጠበትን አርቲክሉን ሆሀተ ያዘጋጀው ከነበረው "ራዕይ" መጽሔት ላይ ጠቅሶ አስነብቦናል፡፡ እኔም በድጋሜ ልጠቅሰው ወደድኩ፡፡ *"... አንድ መካድ የማይቻል ዕዉነታ አለ። ኢትዮጵያ፣ ኤርትራ የምትባል አዲስ ጎረቤት አገር አላት። ይህ ብዙዎቻችን ከራሳችን ጋር እንዲዋሃደን ያልተዘጋጀንበት ዕዉነታ ነዉ። ሊውጡት ያስቸገረ መራራ እንክብል። ለጊዜዉም ቢሆን ከዚህ ዕዉነታ ጋር ራሳችንን ማስታረቅ ካልቻልን ልክ እንደ ሻዕቢያ መሪዎች በሕልም ዓለም ተዘፍቀናል ማለት ነዉ።"* ሐሰን ኡመር አብደላ፣ ራእይ መጽሔት. ሐዳር 1991 ዓ.ም.

ሆሀተ ሆይ... ይሄ የባንዶቹ የነያሲን መሃሙዳ ልጅ አቋም እውነት አንተ ኢትዮጵያዊ ከሆንክ ለኢትዮጵያውያን ምን ይጠቅማል ብለህ ነው አሮጌውን ሰነድ አቧራውን አራግፈህ "ወደዳችሁም ጠላችሁ ተቀበሉት" የምትለን? ወይስ አንተም የጎንደሮቹ ትርምቡሌ ልጆች ልጅ ሁነህ ባንድ ቅኝት ማዝመር ፈልገህን ነውን? ኧረ ባባ ጃሌው ይሁንብህ ተውን አቦ!... ብእርህን ያነሳህበት ጭብጥ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ከቶም ከቶ አስፈላጊ አልመሰለኝም፡፡ የኤርትራዎቹ ባንዶችም ሆኑ የጎንደሮቹ ትርምቡሌዎች ያው ለፍርፋሪ ሲሉ ከጣሊያን ቅኝ ገዢዎች ጫማ ስር ወድቀው ሰሜን አፍሪካንንና ያፍሪካን ቀንድ ሲያምሱ የኖሩ ከሃዲዎች መሆናቸውን ታሪክ ሁሌም ሲያዘክረው ይኖራል፡፡ ምናልባት "ትርምቡሌ" ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለማታውቁት ጥቂት ላብራራ፡፡ ቅኝ ገዢዋ ጣልያን ርካሽ ተዋጊ ወታደሮችና አሽከሮች በቅኝ ግዛትነት ለያዘቻቸው አገሮች ስትፈልግ፤ አስመራ ላይ በነበረው ሹሚ አማካኝነት ከጎንደርና ከጎጃም እየመለመለች ወደ ትሪፖሊ ሊቢያ ትወስዳቸው በነበሩ ቅጥረኖች ስም የተሰየሙ ወታደሮች ናቸው፡፡ እንዲያውም ጎንደሬዎች አንድ ዝነኛ ያዝማሪ ግጥም ነበራቸው፡፡ እንዲህ የሚል...

*"ተእንግዲህ ምላልኝ ጠጁ በብርሌ*
*ግንድ አልብሱ መጣ፣ ሸጋው ጥርንቡሌ"* እያሉ ባዝማሪ ያዘፍኑ ነበር፡፡ ምስጢሩም፣ ጥርንቡሌው ገንዘቡን ጭኖ ከትሪፖሊ ሲመለስ፤ ከበር በመለስ ሁሉንም ጋባዥና አልባሽ ስለነበር ነው... ውዳሴው፡፡

የኢትዮጵያን ትጥቅ አልባ ምስኪን ሕዝብ በተከለከለ የመርዝ ጋዝ ሲያጋዩት መንገድ መሪዎቹና ዋና አስተኳሾቹ የኤርትራ ባንዳዎቹና ትርምቡሌዎቹ ነበሩ፡፡ ታዲያ ያለፈው በደላቸው በዚሁ ቢበቃን መልካም በሆነ ነበር፡፡ እነሱ ግን ያዳቀነው ሰይጣን ሳያቃስሳቸው እንዲለቃቸው ስላልፈለጉ፣ እነየሱፍ ያሲን በነጀብሃ አደራጅነት የጀመሩትን ኤርትራን ከእናት አገሯ ከኢትዮጵያ የመገንጠል የቤት ሥራቸውን የደርግ ዋና ካድሬዎች ሁነው ቀጽለውበት እንደነበር አይዘነጋም፡፡ በደርግ ጉያ ስር ተሸጉጠውም ከነቤተሰቦቻቸው ሲታገሉለት የነበረውን የግንጠላ አጀንዳ ትግባራዊ አድርገዋል፡፡ የቅኝ ገዢው የኢጣሊያ ደጃዝማችነት ሹመት ዳረጎተኛ የነበረው የየሱፍ አባት ያሲን መሃሙዳ፣ በትውልድ መንደሩ በጢዮ በጣገባ ከሚገኘው የዳህላክ ደሴት መሸጎ ኤርትራን ለመገንጠል ለተሰለፈው ለጀብሃ ዓላማ ሲታገል ኖሮ እዚያው ደሴት ላይ ለዘለዓለሙ አሸልቧል፡፡





ላይደረግ በተላሉ ነበር፡፡ ሙሶሎኒ ይህንን በርሀ የሚቆጣጠሩትን ደናክሎች ሳያግባባ ይህን ወረራ ለማካሄድ እንደማይችል በሚገባ ያውቀው ነበር፡፡ ይህንን ችግሩን የፈታው ለፍላጐቱ ተገገር እንዲሆንና አባሪ አጋዥ ኃይል እንዲሆነው መሐመድን በመግዛት ነበር፡፡

በዚህ በገባንበት ቀን ነበር በደስታ እና ትንሽ ኩራ በማለት «የዱቼ» ሰራዊት አደገኛ የሆነውን ጉዞና የተፈፀመውን ሁሉ ያወጉኝ፡፡ በአሀፋው ብዙ ብረት፣ መሳሪያ ለመቀበል ከወራሪው ጦር ጋር ስምምነት ፈጠሩ፡፡ የእሳቸው ግዴታ ሳይታሰብ የጠላት ጦር በዚህ በምስራቁ አቅጣጫ በሚያቋርጠው የአሸዋ ምድር ወደ አዲስ አበባ የሚያደርገውን ጉዞ ማመቻቸትና አቅጣጫ መምራት ነበር፡፡ በዚህም መሰረት ወደ ኢትዮጵያ ዋና ከተማ ለሚደረገው ጉዞ በደስታ ቁጥራቸው 47,000 የሆነ በደንብ የታጠቁና ጠንካራ የተባሉት ወታደሮችና የጦር መኮንኖች ተመርጠው ወደዚህ በረሀ ተላኩ፡፡ ጉዞው በስድስት ምዕራፍ እንዲያልቅ ተመድቦ ስድስት ለመጠጥ የሚሆኑ ጥልቅ የውሃ ጉድጓዶች ራቅ ራቅ ብለው በጉዞ መስመራቸው ላይ ተቆፈሩ፡፡ ጉዟቸውንም የሚመሩ ቃፊሮች ተመርጠው አቅጣጫ እንዲያሳዩዋቸው ተደረገ፡፡

ደጃዝማች መሐመድ በሚስጥር ሁኔታዎችን አመቻቹላቸው፡፡ እንዲመሯቸው የተመደቡት ቃፊሮች በዚህ አስቸጋሪ በርሀ ውስጥ ቀዝቀዝ ባለው በኩል ከአንዱ ነፋሻማ ቦታ ወደ ሌላው በእንክብካቤ እንዲመሩ ተደረገ፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ የጉዞ ምዕራፎች ያለምንም ችግር ተካሄዱ፡፡ የፋሽስት ጦርም ለ47,000 ለተቃጠለና የደረቀን ጉሮሮ የሚያዳርስ በቂ ውሃ ከተቆፈሩለት ጉድጓዶች አግኝቶ ጥሙን ለመቁረጥ እንዲያስችለው «ዱቼ» ጦር በርቱ የሚያስኙና የሰጧቸውን የሮማ መሳሪያዎች በበጐ እንደተቀበሉት የሚገልፅ ጥሩ እንክብካቤ ተደረገላቸው፡፡ በጉዞው ሶስተኛው ምዕራፍ የበረሃው ግማሽ ላይ ሲደርሱ ግን የጦር አለቆቹ በመንገድ መሪዎቹ ሸባ እንደተደረጉና ጉድ እንደሆኑ አወቁት፡፡ አደገኛና ስጋት የሚያሳድር በሆነ ቦታ ዘልቀው ከገቡ በኋላ ወደ ተዘጋጀው ሶስተኛው የውሃ ጉድጓድ ደረሱ፡፡ በውሀውም ውስጥ ለህይወት እጅግ በጣም አደገኛ የሆነ መርዝ እንደተጨመረበት አረጋገጡ፡፡ ወደ አራተኛው የውሀ ጉድጓድ ገሰገሱ፡፡ እዚህም እንደዚሁ አደገኛው መርዝ በሚገባ ተዘጋጅቶ ይጠብቃቸዋል፡፡ ከሰማይ ቁልቁል ቀጥ ብሉ በሚወርደው የአፍሪካ ፀሐይ እና ከምድር በሚነሳው ሙቀትና በሚያቃጥለው አሸዋ መሀል ፍርሀትና ድንጋጤ፣ ትልቅ ትርምስ በመሀላቸው ፈጠረ፡፡ ሁኔታዎች ሁሉ

- 237 -

በኤርትራዊው በያሲን ሙሃሙዳ ጎሳና በኢትዮጵያዊው በቢትወደድ አሊ ሚራህ ጎሳ መካከል ትውልድን አሳልፎ ትውልድን የተካ ግጭትና ጦርነት እንደነበር ዛሬም በሕይወት ያሉ የአፋር አዛውንቶች ይተርኩታል፡፡ ብዙ የሰው እልቂቶች ጦርነቶች ከመካሄዳቸውም በላይ፤ የቤት እንስሳት መዘራረፍና ጠፋቶች ሲደራረሱ ኑረዋል፡፡ የጸባቸው መነሻም ባንዳ ሆኖ ጣሊያንን በማገልገልና ባለማገልገል መሃል የነበረ ያቋም ጥያቄ ነበር፡፡ ያሲን መሃሙዳ ካባቱ በወረሰው ወንበር ለኢጣሊያ ባንዳነት አድሮ፤ አሊ ሚራህን "ለጣሊያን ካልገበርክ አትኖራትም" እያለ ሲያስጨንቃቸው፣ ቆራጡ አሊ ሚራህ በበኩላቸው ”እንኳን እኔ ግመሎቼም ያገራቸውን የኢትዮጵያን ባንዲራ ጠንቅቀው ያውቃሉ” እያሉ እየመለሱ እንዳሳፈሩት በታሪክ ሲነገር ይኖራል፡፡ ታዲያ ቂመኛው ያሲን መሃሙዳ በ2ኛው ዓለም ጦርነት፤ ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በግፍ በወረረችበት ወቅት በባንዳነት ተሰልፎ የነበረው የእሱ ጎሳ ከኤርትራ ተነስቶ በአሰብ በኩል የጣሊያንን ጦር መንገድ እየመራ ወደ አዲስ አበባ ሲገሰግስ፤ እነቢትወደድ አሊ ሚራህ ባንዶቹንና የጣሊያን ወታደሮቹን እንዴት አድርገው ጉድ እንዳደረጓቸው ያይን ምስክሩ ኩባዊ የጦር መኮንን ጽፎታል፡፡ ኩባዊው ኮሎኔል ዴል ባዬ ”ቀይ አንበሳ” ብሎ በጻፈውና ዶ/ር ተስፋዬ መኮንን ባይለየኝ ወዳማርኛ በመለሰው መጽሀፍ ላይ ከገጽ 236-239 ድረስ ይህንን የኢትዮጵያውያን አፋሮችን ወደር የሌለው የጀግንነት ሥራ በሰፊው ተርኮታል፡፡ ስድስት የውሃ ጉድጓድ ቆፍረው፣ መርዝ ጨምረውበት፣ 47 ሺህ የታጠቀ ጠንካራ የኢጣሊያ ጦር የበረሃ ሲሳይ አድርገው ደንከል በረሃ ውስጥ አስቀርተዋል፡፡ የባንዳው መንገድ መሪ ያሲን ሙሃሙዳም ጎሳ በቀልና ቂም በኢትዮጵያውያን አፋሮች ላይ የተተከለ ትውልድ አሳልፎ ትውልድ የተካ ውርዴ ሀሆነኖ ቀርቷል ፡፡

ታዲያ ወደ ”በመመዘኛዋ ኤርትራ ጦስ - ዛሬም ስንተራመስ” ሲል ይሄይስ/ሆህተ ወደ ጻፈው ያድርባይነት ጽሑፍ ስንመለስ፤ የምናነሳው ቁልፍ ጉዳይ አለ፡፡ በዚህ የእከከኝ ልከክህ ጽሑፉ መደምደሚያ ላይ፤ *”እኛ ኢትዮጵያዉያን በቃ ባይዋጠንም የኤርትራን ነፃ አገር መሆን እንቀበል።... የቅኝ ገዥነትና ተገዥነት ታሪኩን አምነን ለመቀበል ለብዙዎቻችን መራር ፅዋ ቢሆንብንም፣ ኢትዮጵያን እንደነሱ እምነት ቅኝ ገዥ አገር አድርገን ብንወስድ እንደ ሌሎች ቅኝ ገዢ አገሮች የጂኦግራፊ ርቀት ባለመኖሩ በኩታ-ገጠምነት በሚኖረን የጧት ማታ ግንኙነት ላይ የተለየ ተፅዕኖ ማሳደሩ ግድ ነዉ።...”* ይለናል፡፡ በዚህ አቋሙም ከኤርትራዊው ባንዳ የሆድ ወዳጁ ከየሱፍ ያሲን አቋምና መስመር ጋር አብሮ ይሰለፋል፡፡ ይሄንን ለእኛ ለኢትጵያውያን ለመንገር ረዥም መንገድ መጓዝና የጫማ ሶሉን መጨረስ ባላስፈለገው ነበር፡፡ ችግሩ የወዳጅ ነገር ሆኖበት እንደሆዳሙ በሬ ሳሩን እንጂ ገደሉን ለማየት አለመቻሉ ነው፡፡ እድሜና ጤና ይስጠውና የኢሳቱ ሲሳይ አጌና የሱፍ ያሲን ኢትዮጵያውያንን በዘርና በጎሳ ለመበታተን አውጥቶና አውርዶ የጻፈውን ርካሽ መጽሐፍ የተንኮል ጭብጥ ተረድቶ፤ ኢሳት ቲቪ ላይ ቃለ መጠይቅ አድርጎለት ባያጋልጠው ኖሮ፤ ስንቱ የዋህ ኢትዮጵያዊ በራሱ ገንዘብ እራሱ የተሰደበበትን ርካሽ ዝባዝንኬ ሸምቶ ያንጀት በሽተኛ በሆነ ነበር፡፡

ሲጀመር ጀምሮ ኤርትራ የምትባል አገር በሕገ ተአምኖ አልነበረችም ወደፊትም አትኖርም፡፡ አራት ነጥብ!!! በሸፍጥና በምእራባዊያን ሴራ እንድትገነጠል መደረጓን ባንዶችና ትርምቡሌዎች (አንተም ሆህተ የደርግ ካድሬ የነበርክ ወጨት ሰባሪነትህ ሳይዘነጋ) ወደ ጎን ትተው፣ ከእግዜር እንደተላከ መና እጃችሁን ዘርግታችሁ የተሠራባችሁን ጭቡ ተቀበሉ ይሉናል፡፡ ከዚህም አልፎ ተርፎ ኢሳት ባዘጋጀወው ጉባዔ ላይ የባንዶቹ ልጆች ተወካይ ”ራሽያን ሩሌት (**Russian roulette** ) ትጫወት ትፈቅድ እንደሁ ናና ሞክረኝና እራስክን በራስህ አጥፋ" እያለ ካንዴም ሁለቴ ይፎክርብናል፡፡ እነየሱፍና ሆህተ ደግሞ ወደዳችሁም ጠላችሁም ይሄ ፎካሪ ሰው የሚላችሁን ተቀበሉ ይሉናል፡፡ አጀብ ነው! እኛው በደገስነው የኢሳት ድግስ ላይ ባንዶቹ አቅራርተውብን፣ ሸልለውብን ሂደዋል፡፡ የመሪያችን የጓድ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ድብቅ ወንድም አይተ ካህሣይ ከበደም ”ዋ ኢሱዬንና ኤርትራን ታሙብኛና ውርድ ተራሴ!...” ብለው አስፈራርተውናል፡፡ እግዜር ይስጠውና ያ ትንታጉ ጋዜጠኛ ደምስ በለጠ በቃሬዛ እንደወጡ ገንዞ ተሃች ተታሪክ መቃብር ቤት አውርዷቸዋል፡፡ ተመስገን - ተመልካች አይጥፋ! ኧረ ስንቱን አንስቼ ስንቱን ልተወው? ”ሆድ ይፍጀው” ነው ያለው ጥልዬ? ይገርማል የዘንድሮ ነገር!!!!